EARLY STAGES
STRONG BEGINNINGS • BRIGHT FUTURES

# የህጻናት ደህንነትና ጥበቃን በተመለከተ የወጡ ደንቦች አጠቃላይ ምልከታ(ጥር 2011 የተከለሰ )

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS
Office of Special Education

በዚህ ወረቀት ላይ ተቀነባብሮ የምታዩት ጽሁፍ በኢ-ጤናማዎች የትምህርት መርሃግብር (Individuals with Disabilities Education Act – IDEA) ስር የተዘረጋው የልዩ ትምህርት ስርአት ሂደት ውስጥ ልጅዎ እና እርሶ ያላችሁን መብት እንድታውቁ ለማስቻል ነው :: ቁልፍ የሆኑ ነጥቦችን ጠቅለል አርጎ ያስቀምጣል :: ነገር ግን በህጉ የሰፈረውን ሁሉንም መብቶች አይገልጽም:: እባክዎን የደህንነት ጥበቃ ደንቦች ሙሉ ጽሁፍ ከ EARLY STAGES መረጃ መረብ ላይ ያንብቡ:: (earlystagesdc.org) ሙሉውን ቅጂ በፖስታ ወይም በኢ-ሜይል ማግኘት ከፈለጉ የ EARLY STAGES ማዕከልን በ 202-698-8037 ደውለው ያሳውቁን :: በደስታ እናስተናግድዎታለን ::

1. **የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA)- እኛ የዲሲ የት/ቤቶች ብለን የምንጠራው ለሁሉም ህጻናት ነጻ እና ተስማሚ ህዝባዊ ትምህርት (FAPE) መስጠት አለበት** :: ይህን ወደ ውጤት ለመቀየር ኢ-ጤናማ የሆን ህጻን ለየት ያለ የትምህርት አሰጣጥ ( የማስተማሪያ ዘዴውን በመለወጥ ማለት ነው ) እና መሰል አገልግሎቶች (ለምሳሌ የንግግር ችግር ህክምና ) ሊያስፈልገው ይችላል :: እነዚህ በዝርዝር በ "ግለኛ የህጻናት ትምህርታዊ ፕሮግራም " (IEP) ላይ ተጽፈዋል ::

2. **ኢ-ጤናማ የሆን ተማሪ በተቻለ መጠን ሙሉ ጤናማ የሆነ ተማሪ በሚማርበት ቦታና አካባቢ መማር አለበት** :: ይህ "እጅግ ዝቅተኛ ገዳቢ አካባቢ " ተብሎ ይጠራል (LRE)

3. ልጅዎ የ "ልዩ የትምህርት ፕሮግራም " እና /ወይም መሰል አገልግሎቶች እገዛ የሚገባው ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ግምገማ ይደረግለታል :: **እርስዎ ለልጅዎ በሚደረገው የችግር መለያ ,የግምገማ እና የትምህርት ምደባ ላይ ሁሉ የመገኘት መብት አሎት** የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ከመነሻው ሲያቅድና ወደ ድርጊት ሲያሸጋግር ሊያሳውቆት ይገባል :: ይህንን የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወሻ እንለዋለን :: (ገጽ 7)

4. **የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ግምገማውን ከመጀመሩ በፊት እና አስከትሎም ልዩ የትምህርት ስልጠናና መሰል አገልግሎቶች ከመሰጠቱ አስቀድሞ የእርስዎ እውቂያ እና የጽሁፍ ፍቃድ አስፈላጊ ነው :: የእርስዎ ስምምነት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ እና በፈለጉት ጊዜ ( ይህ ቀድሞ የተስማሙበት ቢሆንም እንከዋን ) ሊሰርዙት ይችላሉ** :: ሲሰርዙት ታዲያ በጽሁፍ ፊርማዎን እና ቀኑን አስፍረው ነው ::(ገጽ 9-10)

5. **ያለምንም ክፍያ ነጻና ገለልተኛ ትምህርታዊ የሆነ ግምገማ ሊጠይቁ ይችላሉ** :: (IEE) የጥያቄዎ መነሻ ታዲያ በአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ የተከናወነው ግምገማ ያልተስማማዎት ሲሆን ነው ::

6. የአካባቢው የትምህርት ማእከል ልጅዎን አስመልክቶ (1) የተለየ የትምህርት ስልጠናና መሰል አገልግሎቶች ላይ በሰጠው ውሳኔ (2) በአጠቃላይ ግምገማው ላይ (3) የአገልግሎቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆን በተመደበበት ቦታ ላይ ወይም (4) በአጠቃላይ ለነጻና ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት የማግኘት መብቱን በሚመለከት የማይስማሙበት ነገር ካለ **ቅሬታዎን አቅርበው የመደመጥ መብትዎን ሊጠቀሙ ይችላሉ** ::(ገጽ 19)

7. **የልጅዎ የትምህርት ቤት ማህደር (Record) ኮፒዎች የመቀበል መብት አለዎት** :: በማህደሩ ላይ የሰፈረው ስህተት ነው ብለው ካመኑ ትምህርት ቤቱ እንዲለውጠው የመጠየቅ መብት አለዎት (ገጽ 13-14)

## ኢ-ጤናማ የሆነ ህጻን የትምህርት ቤት ስርአት እና ደንብ የጣሰ እንደሆነ

የህጻኑ ባህርይ ከጤንነት ችግር ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልጽ ከሆነ ,ህጻኑ ከትምህርት ማእከሉ አስር እና ከዚያ በላይ ለሆነ የትምህርት ቀናት ላይባረር ይችላል :: ይህ ለህጻኑ የሚደረግለት ጥበቃ የሚጀምረው ህጻኑ ኢ- ጤናማ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወዲያው የግምገማ ሂደቱ እንደጀመረ ነው :: ለኢ- ጤናማ ህጻናት ሌሎች ተመሳሳይ ጥበቃዎች ይደረግላቸዋል :: ክልከላ የሚፈልጉ ለየት ያሉ ሁኔታዎችም አሉ :: የልጅዎ ባህርይ እንግዳ ከሆነብዎት እና የትምህርት ቤቱም ምላሽ አሳሳቢ ከሆነብዎት እነዚህን ገጾች (29-34) በትኩረት ያንብቧቸው ::